በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION DIRECTORATE

ቁጥር የሕ/ም/ማጠ/ዳ/...ዐ2ፈ2ፈ118

ቀን 23/04/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ስራና ክህሎት ቢሮ
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ1 (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት የስራና ክህሎት ቢሮ በቁጥር ስ/ለ/ም/ቢ/4/ሚ/85/371 በቀን 30/01/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የመንግስት ፖሊቴክኒክና የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የማታ ትምህርትና ስልጠና ማስተግበሪያ መመሪያ" ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 23/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲወል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ...16.....ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

'ከሰላምታ ጋር'

ሺድጋፍ ኃይሌ
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

16

# በአብክመ የቴክኒክ ሙያና ኢንርፕራይዞች ልማት ቢሮ የማታ ትምህርትና ስልጠና ማስተግበሪያ መመሪያ

የካቲት 2011 ዓ.ም

ባህር ዳር

## መመሪያ ቁጥር 23/2018

# በቴክኒክ ሙያና ኢንርፐራይዞች ልማት ቢሮ የማታ ትምህርትና ስልጠና ማስተግበሪያ መመሪያ

በአብክመ የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፐራይዞች ልማት ቢሮ ስራ በሚገኙ የፖሊቴክኒክና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የማታ ትምርትና ስልጠና ማስፈጸሚያነት እንዲያገለግል በ2002 ዓ.ም መመሪያ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል መደረጉ ይታወሳል፡፡ መመሪያው ግልጸኝነት የጎደለውና ዝርዝር ሁኔታዎችን ያላካተተ በመሆኑ እየተካሄደ በነበረው የማታ ትምህርትና ሥልጠና ላይ በርካታ ችግሮች ተከስተዋል፡፡ ከነዚህ ችግሮች መካከልም፡-

- በማታ ትምህርት ገቢ አሰባሰብና በማታ ትምህርትና ሥልጠና ስራ ላይ ከሚሳተፉ አሰልጣኝ መምህራንና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ክፍያ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቅሬታዎች በመኖራቸው፣
- የማታ ትምህርትና ስልጠና እንደቀኑ ሥልጠና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን የሚከታተል የውስጥ ሱፐርቫዘር በማስፈለጉ፣
- ኃላፊነትና የሥራ ድርሻን እንዲሁም የአሰራር ሥርዓትን በሚመለከት ክፍተቶች በመታየቸው፣
- በማታው ትምህርት የሚሳተፉ ዲኖችና ም/ዲኖች፤ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች፤ የአሰልጣኞችና ኢንስትራክተሮች እንዲሁም የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተግባርና ኃላፊነት ተለይተው ባለመቀመጣቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታትና በአሁኑ ወቅት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከገበያ ፍላጎት እንጻር ስልጠና የሚሰጥባቸው የሙያ መስኮች በመስፋታቸው በነዚህ ሙያዎች ከደረጃ 1 እስከ 5 ገብቶ ስልጠናውን በመከታተል የሙያ ባለቤት ለመሆን የሚፈልገው የህብረተሰብ ክፍል ቁጥሩ እያደገ በመምጣቱ ይህን ለማስተናገድ የሚያስችል የማታ ትምህርትና ስልጠና ማስተግበሪያ መመሪያ ማዘገጀት አስፈልጓል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴክኒክና ኢንተርፕራዞች ልማት ቢሮ የመንግስት ፖሊቴክኒክና የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የማታ ትምህርትና ስልጠና ማስተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 23/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 "የማታ ትምህርትና ስልጠና" ማለት መደበኛ የቀን ትምህርትና ስልጠና" ከሚካሄድበት ጊዜና ሰዓት ውጭ በምሽት እና በሣምንቱ የመጨረሻ ቀናት ቅዳሜና እሑድ የሚካሄድ ትምህርትና ስልጠና ነው፡፡

2.2 "አሰልጣኝ መምህር" ማለት በማታው ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ውል ገብቶ የተመደበና የአሠልጣኝነት/ኢንስትራክተርነት ማዕረግ ያለው፣ ኮሌጁን በዲንነት ወይም በምክትል ዲንነት በመምራት ላይ ያሉ፣ የማታውን ትም/ስልጠና ፕሮግራም እንዲመራ የተወከለ አስተባባሪ፤ ስልጠና የሚሰጥባቸው ሙያዎች ዘርፍ ኃላፊዎች ማለት ነው፡፡

2.3 "ሰልጣኝ" ማለት በማታው ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የመግቢያ መስፈርቱን በማሟላት ኮሌጁ ተቀብሎት በመሰልጠን ላይ የሚገኝ ማለት ነው

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የማታ ትምህርትና ስልጠና አተገባበር መመሪያ ተፈፃሚነት የሚኖረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር በሚገኙ የመንግስት ፖሊቴክኒክ ኮሌጆችና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

## 4. አደረጃጀት

4.1 የማታ ትምህርትና ሥልጠና በክፍል ደረጃ ተደራጅቶ ትምህርትና ስልጠናውን የሚመራ ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5.4 መሠረት ለክፍሉ የተሰጡትን ኃላፊነትና ተግባር እንዲያስፈጽም በባህሪው ለሌሎች አርአያ የሆነ እንዲሁም በአሰልጣኝነትና በአስተባባሪነት የተሻለ ልምድ ያለው ተጠሪነቱ ለኮሌጁ ዲን የሆነ አሰልጣኝ መምህር በቀጥታ በኮሌጁ ዲን ተመድቦ የማታ ትምህርት ክፍሉን በአስተባባሪነት ይመራል፡፡

4.2 ተጠሪነታቸው ለትምህርትና ለማታ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪ የሆኑ በማታው ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ስልጠና የሚሰጥባቸው ሙያዎች የዘርፍ አስተባባሪዎች (Department Heads) የየራሳቸውን ዘርፍ የሚመሩ ሆነው በዚህ መመሪያ 5.5 የተዘረዘሩ ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

4.3 የማታ ትምህርትና ሥልጠና እንደቀኑ ሥልጠና ደረጃውን ጠብቆና የሚፈለገውን ስታንዳርድ አሟልቶ የሚካሄድ መሆኑን የድጋፍና ክትትል ስራ የሚያከናውን ከየስልጠና ዘርፉ የተውጣጣ የውስጥ የሱፐርቪዥን ቡድን ይደራጃል፡፡

## 5. ተግባርና ኃላፊነት

5.1 የኮሌጁ ዲን ተግባርና ኃላፊነት

5.1.1 በአጠቃላይ የማታ ትምህርትና ሥልጠናን በበላይነት ይከታተላል ይመራል፣

5.1.2 በማታው ትምህርትና ስልጠና የስልጠና ዘርፍ አስተባባሪዎችም ሆነ በትምህርትና ስልጠና ቡድን መሪና ም/ዲን ደረጃ መፍትሔ ሊያገኙ ያልቻሉ ጉዳዮችን መርምሮ መፍትሔ ይሠጣል፤

5.1.3 ከአሠልጣኝ መምህራንም ሆነ ከማታ ሠልጣኞች የሚነሱ የተለያዩ ቅሬታዎችንና ችግሮችን በመቀበል የማታ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ አስተባባሪዎችና የትምህርትና ስልጠና ቡድን መሪና ም/ዲንን በማወያየት ጭምር መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ውሣኔዎችን ያስተላልፋል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ይደረጋል፣

5.1.4 በአጠቃላይ የማታ ትምህርትና ሥልጠና መመሪያንና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂን መሠረት አድርጎ የሚካሄድ መሆኑን ይከታተላል ክፍተቶች ከታዩም ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በመመካከር የመፍትሄ ሀሣቦችን ያቀርባል ተቀባይነት ሲያገኝም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

5.2 የትምህርትና ስልጠና ቡድን መሪና ም/ዲን ተግባርና ኃላፊነት

5.2.1 የማታ ትምህርትና ስልጠናን ያስተባብራል ይመራል፣

5.2.2 የማታ ት/ሥልጠና ክፍል አስተባባሪ የሚያቀርባቸውን ጉዳዮች ይመረምራል ይወስናል፤ እንዲሁም አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችን ከማታ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪና ከዘርፍ ኃላፊዎች ጋር በመወያየት ውሳኔ እንዲያገኙና ውሣኔውም በዲኑ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

5.2.2 በማታ ትምህርትና ስልጠና ሥራ ለተሳተፉ ሰራተኞች በየወሩ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት አግባብነቱን ያረጋግጣል፣

5.2.3 በማታ ትምህርትና ስልጠና ላይ የሚታዩና እየተንከባለሉ የመጡ ችግሮች እንዲጠኑ ያስተባብራል፣ የመፍትሔ ሃሣቦችንም ያመነጫል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

5.2.4 በማታ ትምህርትና ስልጠና ላይ የሚሳተፉ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል ችግሮችም ሲከሰቱ አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

5.2.5 ሥልጠናውን በየጊዜው ይከታተላል የተሻሉ መንገዶችንም ይቀይሳል፣

5.2.6 የሥልጠና ግብዓት መሟላቱንና የሥልጠና ምቹነትን ያረጋግጣል፤

5.2.7 በአጠቃላይ የማታ ትምህርትና ሥልጠና መመሪያንና የቴክኒክና ሙያ ት/ሥልጠና ስትራቴጂን መሠረት አድርጎ የሚካሄድ መሆኑን ይከታተላል ያረጋግጣል፣

5.2.8 የስልጠና ግብዓት መሟላቱንና የሥልጠና ምቹነትን ያረጋግጣል።

5.3 የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ቴክ/ሽግግር ቡድን መሪና ም/ዲን ተግባርና ኃላፊነት

5.3.1 የማታ ትምህርትና ስልጠናን በተተኪነት ይመራል፣

5.3.2 በማታው ትምህርትና ሥልጠና ላይ የሚታዩና እየተንከባለሉ የመጡ ችግሮች እንዲጠኑ ያስተባብራል፣ የመፍትሔ ሃሣቦችንም ያመነጫል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

5.3.3 የማታ ት/ሥልጠና ክፍል አስተባባሪ የሚያቀርባቸውን ጉዳዮች ይመረምራል ይወስናል፤ እንዲሁም አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችን ከማታ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪና ከዘርፍ ኃላፊዎች ጋር በመወያየት ውሳኔ እንዲያገኙና ውሳኔውም በዲኑ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

5.3.4 የማታው ትምርትና ስልጠና በየሙያ ደረጃው ስልጠናው ፕሮጀክት ተኮር ስልጠና መሆኑን ይከታተላል፤ በየወሩ ስለተግባሩ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

5.3.5 በማታው ትምህርትና ስልጠና ላይ የሚሳተፉ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ከታተላል፤

5.2.7 በአጠቃላይ የማታ ትምህርትና ሥልጠና መመሪያንና የቴክኒክና ሙያ ት/ሥልጠና ስትራቴጂን መሠረት አድርጎ የሚካሄድ መሆኑን ይከታተላል ያረጋግጣል፣

5.4 የማታ ትምህርትና ሥልጠና አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት

5.4.1 ለማታ ሠልጣኞች መርሐ ግብር በማውጣት ምዝገባ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

5.4.2 የማታ ት/ሥልጠና ዓመታዊ ካሌንደር መመሪያን ባገናዘበ መልኩ ያዘጋጃል፤

5.4.4 በማታው ት/ሥልጠና ኘሮግራም የሚሳተፉ አሠልጣኝ መምህራንንና ሾፕ ቴክኒሻኖችን ከዘርፍ ኃላፊዎች ጋር በመሆን የሥራ ሥነ-ምግባርና ብቃትን መሠረት ባደረገ መልኩ በመለየትና የውል ግዴታ በማስፈረም ወደ ሥራ ማስገባት፣

5.4.5 በማታው ኘሮግራም አዲስ የሚከፈቱ የሥልጠና መስኮችን በሚዲያና በውስጥ ማስታወቂያዎች በማስተዋወቅና በመጋበዝ መስፈርቱን የሚያሟሉት ተመዝግበው ቁጥራቸው በደንቡ መሠረት በቂ ሆኖ ሲገኝ ወደ ሥልጠና እንዲገቡ ማድረግ፣

5.4.6 የሥልጠና ዘርፎች አዘጋጅተው በሚያቀርቡት ዕለታዊና ሳምንታዊ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የሥልጠና ሂደቱንና ተሳታፊዎችን ዕለት ተዕለት ይቆጣጠራል፣

5.4.7 በተደጋጋሚ የሥራ ዲሲኘሊን ችግር የታየበትን አሠልጣኝ ለትምህርትና ስልጠና ቡድን መሪና ም/ዲን ሪፖርት በማቅረብና ከዘርፍ ኃላፊም ጋር በመነጋገር በምትኩ ሌላ አሠልጣኝ እንዲተካ ማድረግ፣

5.4.8 በማታው ት/ሥልጠና ኘሮግራም የሚሣተፉ ድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል በየወሩም ሪፖርት ያቀርባል፣

5.4.9 የማታ ሠልጣኞች ወርሃዊ ክፍያ የሚከፍሉበትን ኘሮግራም ያወጣል፣ በኘሮግራሙ መሠረት ያልከፈሉት ቅጣትን ጨምረው እንዲከፍሉ ያደርጋል እንዲሁም ከ2 ወር በላይ የተወዘፈበት ሠልጣኝ ሥልጠናውን እንዲያቋርጥ ያደርጋል፣

5.4.10 እያንዳንዱ የሥልጠና ወር እንዳለቀ በወር ውስጥ የተሠራውን ክፍል ጊዜ አሰልጣኝ መምህራን እንዲያዩት በግልጽ ቦታ ይለጠፋል፣ ቅሬታም ካለ በአግባቡ ያስተናግዳል፣ በመቀጠልም በሥራው ለተሣተፉት ወርሃዊው ክፍያ ቀጣዩ ወር በገባ በ5 ቀን ውስጥ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

5.4.11 በማታው ኘሮግራም የሚያሠለጥኑ መምህራን እያንዳንዱ የብቃት አሀድ /Unit of competence/ እንደተጠናቀቀ የምዘና ውጤት ማስገባታቸውን ከዘርፍ ኃላፊዎች ጋር ያረጋግጣል፣ በወቅቱ ሊያስገቡ ያልቻሉ አሠልጣኞችን ዝርዝር ሪፖርት በማድረግ ወርሃዊ ክፍያም ጭምር ተይዞ ውጤት እንዲያስገቡ ያደርጋል፡

5.4.12 አጠቃላይ የማታ ት/ሥልጠናን በሚመለከት በየወሩ ለትምህርትና ሥልጠና ቡድን መሪና ም/ዲን ሪፖርት ያቀርባል፣

5.4.13. የሠልጣኞች መብትና ግዴታ በአግባቡ መፈፀሙን መከታተል፣ መገምገምና ለሚመለከተው ማሣወቅ

5.4.14 ከኮሌጁ የበላይ አመራር የሚሠጡትን ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናል፡፡

5.5 የትምህርትና ሥልጠና የዘርፍ ተጠሪዎች (Department Heads) ተግባርና ኃላፊነት

5.5.1 የማታው ትምህርትና ስልጠና ክፍል የቅበላ አቅም ማለትም ሊከፈቱ የሚችሉ የሙያ መስኮችንና ደረጃዎችን እንዲሁም የሠልጣኝ ቁጥር በየደረጃው ምን ያህል መሆን እንዳለበት ለአስተባባሪና ለት/ም/ስልጠና ም/ዲን ከምዝገባ ጊዜ ቀደም አድርጎ በዝርዝር ማሳወቅና በጋራ ውሣኔ ላይ እንዲደረስ ማድረግ፣

5.5.2 በማታው ትምህርትና ስልጠና ለመሳተፍ ከሚያመለክቱ መምህራን መካከል የተሻለ የሥራ አፈፃፀም፣ ብቃትና የሥራ ሥነ-ምግባር ያላቸውን በመለየት የአሠልጣኝነት ማዕረጋቸው

በሚፈቅደው ደረጃ መመደብና የስልጠና ኘሮግራም በማውጣት ለአሰልጣኝ መምህራንና ለአስተባባሪ ያሣውቃሉ፣

5.5.3 በማታው የሥልጠና ኘሮግራም የሚሰጡ የብቃት አሃዶች /Units of Competence/ በተቀመጠላቸው ሰዓት መከናወናቸውን ይቆጣጠራል፤ ክፍተቶች ሲታዩም በፍጥነት እንዲስተካከሉ ያደርጋሉ፣

5.5.4 የዲፓርትሜንት ኃላፊዎች የዓመቱ ስልጠና እንደተጀመረ ለሁሉም የሙያ ደረጃዎች የተቀመጡ የብቃት አሃዶች /Units of Competence/ በማን እንደሚሰጡና ከመቼ እስከ መቼ እንደሚሰጡ በጥንቃቄ ምደባና ድልደላ በማካሄድ ለማታ ትምህርት አስተባባሪና ለሬጅስትራር ያሳውቃሉ፣

5.5.5 በየጊዜው በሠልጣኞች የሚነሱ ቅሬታዎችን ከሥልጠና አስተባባሪ ጋር በመሆን ያጣራሉ መፍትሔም ይሰጣሉ፤ በእነሱ ደረጃ የማይፈታ ከሆነ ለትምህርትና ስልጠና ም/ዲን ሪፖርት ያደርጋሉ፣

5.5.6 አሠልጣኝ መምህራን የሚሰጡትን የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠናዎችን እና ምዘናዎችን ይከታተላሉ፣ ተከታታይ ግምገማ ያካሂዳሉ እንዲሁም የማሻሻያ ሥራዎችንም ከአሰልጣኝ መምህራን ጋር ያከናውናሉ፡

5.5.7 እያንዳንዱ የብቃት አሃድ /Unit of Competence/ እንደተጠናቀቀ የምዘና ውጤት ከአሠልጣኝ መምህራን በመረከብ ለሬጅስትራር ክፍል ገቢ ያደርጋሉ፣ የማያስረክቡ አሰልጣኝ መምህራን በጊዜ ገደብ ማስጠንቀቂያ ተሠጥቷቸው እንዲያስገቡ ሆኖ ካላስገቡ ቀጣዩን የብቃት አሃድ እንዳያሠለጥኑ ለሥልጠና አስተባባሪና ለትምህርትና ስልጠና ም/ ዲን ሪፖርት ያደርጋሉ፣

5.5.8 በተጨማሪ ከሥራ ሃላፊዎች የሚሠጡ ሌሎች ሥራዎችን በአግባቡ ያከናውናለ።

5.5.9 የማታ ትምህርትና ስልጠና በአግባቡ ስለመካሄዱ የሱፐርቪዥን ስራ ይሰራሉ። ለዚህም የሚከተሉት ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

- የማታ ትምህርትና ሥልጠና ከቀኑ ባላነሰ ሁኔታ ደረጃውን ጠብቆ መሰጠቱን ይቆጣጠራሉ፣

- ለማታ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም መጠናከር ሙያዊ እገዛና ድጋፍ ይሠጣሉ፣
- በማታ ትምህርትና ሥልጠና ሂደት የአሠልጣኞችንና የሠልጣኞችን ግንኙነት በቅርብ ይከታተላሉ፡
- ሥልጠናው በመመሪያና በስትራቴጂው መሠረት ስለመሆኑ ይቆጣጠራሉ፣
- የሚሠጡ ምዘናዎችና የሚያዙ ውጤቶች ተገቢውን አሠራር የተከተለና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን የቅርብ ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

5.5.10 ከኮሌጁ የበላይ አመራር የሚሰጡዋቸውን ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናሉ፡፡

5.5 የአስልጣኝ መምህራን ተግባርና ኃላፊነት

5.5.1 በማታው ትምህርትና ስልጠና ለመሳተፍ ማመልከት፣ ከስልጠና ዘርፍ ኃላፊ ይሁንታ ማግኘትና ኮሌጁ ያዘጋጀውን ውል በመፈረም የውል ግዴታ መግባት ያስፈልጋል፣

5.5.2 የኮሌጁ አሠልጣኝ መምህራን የሠለጠኑበትን የሙያ መስክና የአሰልጣኝነት ደረጃቸውን መሠረት ባደረገ መልኩ ማሰልጠን በሚገባቸው የሙያ መስክና ደረጃ መመደብ ይኖርባቸዋል፣

5.5.3 በማታው የሥልጠና መርሀ-ግብር የሚያሰለጥኑ አሰልጣኝ መምህራን በወጣላቸው ኘሮግራም መሠረት ሰዓት ሳይሸራረፍ በወቅቱ በመገኘት ትምህርትና ስልጠና መስጠት ይኖርባቸዋል፣

5.5.4 አሠልጣኝ መምህራን ሁሉንም የብቃት አሐዶች /Units of Competence/ በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ ብቻ ማጠናቀቅና ያልበቁትን ሠልጣኞች ጎን ለጎን እስከ ሁለት ጊዜ ድረስ ድጋፍ በማድረግ ማብቃት ይኖርባቸዋል፣

5.5.5 አሠልጣኝ መምህራን እያንዳንዱ የብቃት አሀድ /Unit of Competence/ እንደተጠናቀቀ የተቋም ውስጥ ምዘና ውጤት ለዲፓርትሜንት ኃላፊዎች ገቢ ያደርጋሉ የዲፓርትሜንት ኃላፊዎችም በተመሣሣይ ሁኔታ ለሬጅስትራር ክፍል ማስገባት ይኖርባቸዋል፣

5.6.6 አሠልጣኝ መምህራን በኮሌጁ ዓመታዊ የስልጠና ካሌንደር መሠረት የመጨረሻውን የማታ ክፍያ ማግኘት የሚችሉት ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆናቸው ክሊራንስ ሲያቀርቡ ብቻ ይሆናል፣

5.5.7 የሥልጠና አስተባባሪዎች በየሙያ መስካቸው የአሰልጣኝነት ማዕረጋቸው በሚፈቅደው ደረጃ ሥልጠና መስጠት ይችላሉ፣

5.5.8 ዲኖች፣ ም/ዲኖችና የዘርፍ አስተባባሪዎች አሠልጣኝ መምህራን ስለሆኑ በሙያቸው ማሠልጠን ይችላሉ፤

5.5.9 ማንኛውም በማታው መርሀ ግብር ስልጠና ለመውሰድ የተመዘገቡ ሰልጣኞች ያሉበት የሙያ ደረጃ የሚያሰልጥን አሰልጣኝ መምህር የማሰልጠን ግዴታ አለበት፤

5.5.10 የማታው ክፍለ ጊዜ አሠልጣኞች ከሥራ ኃላፊዎች የሚሠጡ ሌሎች ተግባራትንም ያከናውናሉ፣

5.6 የሾፕ ቴክኒሽያን ተግባርና ኃላፊነት

5.6.1 የዕለቱ ሥልጠና ከመጀመሩ ከ30 ደቂቃ በፊት በመገኘት ወርክሾፖችን በመክፈት አልጣኞቹ የሚፈልጉትን ዕቃዎችን ያዘጋጃል፣

5.6.2 ስልጠና እስኪጠናቀቅ በወርክ ሾፕ የመቆየት ግዴታ አለበት፣

5.6.3 ለአሰልጣኞችና ኢንስትራክተሮች በትውስት የሚሰጣቸውን መሣሪያዎች አንድ በአንድ ቆጥሮ የማስረከብና የመረከብ ኃላፊነት አለበት፤

5.6.4 በማታው ፕሮግራም በሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና ተገኝቶ ሥልጠናው የተቀላጠፈ እንዲሆን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፤

5.6.5 የሾፕ ቴክኒሽያን ላልተገኘባቸው/አገልግሎት ላልተሰጠበት ቀን ክፍያ አይፈጸምም፤

5.6.6 በትምህርት ክፍሉ ለሚገኙ ንብረቶች ደህንነት መጠበቅ የተሰጠው ኃላፊነት ከፍተኛ በመሆኑ የጠበቀ ችግር ሲገጥመው ለሚመለከተው አካል በፍጥነት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

5.6.7 የሚሠጣቸውን አገልግሎቶች በሚመለከት ከኮሌጁ ጋር የውል ግዴታ ይገባል፣

5.6.8 ችግር ሲያጋጥመው የሥልጠና ሰዓት ከመድረሱ በፊት ለሚመለከተው ሪፖርት ማድረግ አለበት፣

5.6.9 በትምህርት ክፍሉ ኃላፊ የሚሰጡትን ተጨማሪም ሥራዎችንም በአግባቡ ያከናውናል

## ክፍል ሶስት

## የማታ ሠልጣኞች አቀባበል እና የሚከፍሉት ክፍያ

### 6. የማታ ሰልጣኞች አቀባበል

6.1 የአዲስ ሰልጣኞች አቀባበል በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ እና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ በቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ለትምህርትና ስልጠና ዘመኑ በተቆረጠው የመግቢያ መስፈርት መሠረት ሆኖ በቴክኒኩ ዘርፍ(Hard Skill) ሙያዎች በአንድ የሥልጠና ክፍል ውስጥ ቁጥራቸው ከ25 እስከ 30 በሆነ ሠልጣኝ ስልጠና መጀመር ይቻላል፣

6.2 ከዚህ በላይ በቁጥር 6.1 የተመለከተው ለነባር ሰልጣኞችም ተፈፃሚ ይሆናል፣

6.3 በመሰልጠን ላይ የሚገኙ ነባር ሰልጣኞችን በሚመለከት ቁጥራቸው ከ20 በታች ከወረደ አዋጪ ስለማይሆን ከ20 የሚጎድለውን ሰልጣኝ ክፍያ ልዩነት የቀሩት ተካፍለው ለመሸፈን ተስማምተው ውል ከፈረሙ ብቻ ስልጠናው ሊካሄድ ይችላል፣

6.4 የተመሣሣይ ሙያና ደረጃ ሠልጣኝ ሆነው በሁለት እና ከዚያ በላይ ሴክሽን ውስጥ የሚሠለጥኑ ተማሪዎች ቁጥራቸው ሲቀንስ ወደ አንድ ሴክሽን ተጠቃልለው እንዲሠለጥኑ ይደረጋል፣

6.5 የሥልጠና ጊዜን በሚመለከት በሁሉም የሥልጠና መስክ በሣምንት ማሠልጠን የሚቻለው 20 ክፍለ ጊዜ ብቻ ሆኖ የእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1፡00 ሰዓት ይሆናል፡

6.7 ለሁሉም የሥልጠና መስኮች በየቀኑ ሁለት ክፍለ ጊዜ የሚኖራቸው ሲሆን ሥልጠናውም የሚካሄድበት የመግቢያ ሰዓት ምሽት 12:00 ሰዓት ሆኖ የመውጫው ሰዓት ከምሽቱ 2፡ 00 ይሆናል፡፡

6.7 የማታው ትምህርትና ስልጠና ቅዳሜ እና እሁድን ሚጨምር ከሆነ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ እንደ መደበኛው(የቀን) ስልጠና ፕሮግራም ተመሳሳይ ይሆናል፤

6.8 የእያንዳንዱን ሥልጠና ደረጃ ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ በተቀመጠው የስልጠና ሰዓት/Nominal Duration/ ርዝማኔ እና በሰልጣኞች ሙብቃት ይወሰናል፤

## 7. የማታ ሰልጣኞች የሚከፍሉት ክፍያ

7.1 አዲስ ገቢ ሠልጣኞች ለሚያመለክቱበት የሙያ መስክና ደረጃ የተቀመጠውን የመግቢያ መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ የመመዝገቢያ ብር 50 እና ለደረጃው የተቀመጠውን የመጀመሪያ ወር ክፍያ በመፈፀምና የውል ግዴታ በመግባት ሥልጠና ይጀምራሉ፣

7.3 ሁሉም የማታ ሠልጣኞች ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ወርሃዊ ክፍያቸውን

መፈፀም ይጠበቅባቸዋል:-

- የወርሃዊ ክፍያ ጊዜ ወር በገባ እስከ 5 ድረስ ያለቅጣት ይከፈላል፣
- ወር በገባ ከ6 እስከ 10 ድረስ ከብር 25ቅጣት ጋር ይከፍላሉ፣
- ወር በገባ ከ11 እስከ 15 ድረስ ከብር 35 ቅጣት ጋር ይከፍላሉ፣
- ወር በገባ ከ16 እስከ 20 ድረስ ከብር 45 ቅጣት ጋር ይከፍላሉ፣
- ወር በገባ ከ21 እስከ 30 ድረስ ከብር 55 ቅጣት ጋር ይከፍላሉ፣
- ከአንድ ወር በላይ እየተወዘፈ ሲሄድ ማስጠንቀያ ይሰጣቸዋል፤ ለ2 ወር የህል ወርሀዊ ክፍያ ሳይከፍሉ ሲቀር ከስልጠና ይታገዳሉ፤

7.4 ለሁሉም የሙያ ደረጃዎች የማታ ሠልጣኞች የሚከፍሉት ወርሃዊ ክፍያ ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የማታ ትምህርትና ሥልጠና ገቢዎች እና የገቢዎች ክፍፍል

### 8. የማታ ትምህርትና ሥልጠና ገቢዎች

8.1 ከማታ ትምህርትና ሥልጠና ሠልጣኞች የሚሰበሰብ የመመዝገቢያ ክፍያ፣

8.2 ከማታ ትምህርትና ሥልጠና ሠልጣኞች የሚሰበሰብ መደበኛ ወርሃዊ ክፍያ፣

8.3 ከማታ ትምህርትና ሥልጠና ሠልጣኞች የሚሰበሰብ የቅጣት ክፍያ ናቸው።

9. የማታ ትምህርትና ሥልጠና ጥቅል ገቢ ክፍፍል

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ተራ ቁጥር 8.1፣ 8.2 እና 8.3 የተመለከተውና በየወሩ ከማታ ሠልጣኞች ከሚሰበሰበው ጥቅል ገቢ ላይ 30% ለኮሌጁ ውስጥ ገቢ ሆኖ ለማታ ሥልጠና ግብዓትና ለተያያዥ ወጪዎች የሚውል ይሆናል። ከጥቅል ገቢው 60% በማታው ትምህርትና ሥልጠና ለሚሣተፉ ዲኖችና ም/ዲኖች፤ የማታ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪዎች፤ የስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች፣ አሰልጣኝ መምህራን የሚከፈል ሲሆን ከጥቅል ገቢው 10% ለድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ክፍያ የሚውል ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## በማታ ትምህርትና ስልጠና የሚገኘው ገቢ ክፍፍል

10. የኮሌጁ ድርሻ

ከላይ በተራ ቁጥር 9 ላይ እንደተገለጸው ከማታ ትምህርት ከሰልጣኞች ከምዝገባ፣ ከወርሀዊ ክፍያና ከቅጣት በየወሩ ከሚሰበሰበው አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 30 ፐርሰንቱ ለማሰልጠኛ ጥሬ ዕቃ ግዥ፣ ለውሀና ለመብራት ፍጆታ እና ለማሽን ድፕርሴሽን ይውላል፡፡

11. በማታው ትምህርትና ስልጠና ለሚሣተፍ የሰው ኃይል የሚደረግ ክፍያ

11.1 ለአሠልጣኝ መምህራን የሚደረግ ክፍያ

11.1.1 የአሠልጣኝ መምህራን ክፍያ የሚውለው በማታው ትምህርትና ስልጠና እንዲያስለጥኑ ለተመደቡ አሰልጣኝ መምህራን ነው፡፡ ክፍያው የሚፈጸመው እንዳንዱ አስልጣኝ መምህር በወር ውስጥ በሚያስለጥነው ክፍለ ጊዜ መጠን ሲሆን አንድ አሠልጣኝ መምህር በሣምንት ማሠልጠን የሚችለው ከፍተኛው ከ20 ክፍለ ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

11.1.2 ለማታ ትምህርት ከሰልጣኞች ከተሰበሰበው አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 60 ፐርሰንቱ በማታው ፕሮግራም ስልጠና ለሚሰጡ አሰልጣኝ መምህራን፣ ዲኖች፣ ም/ዲኖች ለማታ ትም/ስልጠና አስተባባሪዎች፣ ለስልጠና ዘርፍ ኃላፊዎችና ሾፕ ረዳቶች ክፍያ ይውላል፤

11.1.3 ለአሰልጣኝ መምህራን ዲኖች፣ ም/ዲኖች፣ የማታ ትም/ስልጠና አስተባባሪዎች፣ ለስልጠና ዘርፍ ኃላፊዎችና ሾፕ ረዳቶች በክፍለ ጊዜ የሚከፈለው ገንዘብ መጠን የተቆረጠ (Fixed) ሳይሆን በየወሩ ከማታ ሠልጣኞች በሚሰበሰብ ገንዘብ መጠን ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

11.1.4 ለአሰልጣኝ መምህራን ከማታ ትምህርት ገቢ ለሰዓት የሚከፈለው ገንዘብ የአሰልጣኝነት ማዕረጋቸው መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ለ'ሲ' ደረጃ አሰልጣኞች በሰዐት 35 ብር፤ ለ'ቢ' ደረጃ ኢንስትራክተሮች 45 ብር፤ ለ'ኤ' ደረጃ ኢንስትራክተሮች 55 ብር ይሆናል፤

11.1.5 ከላይ በተራ ቁጥር 11.1.1 እና 11.1.2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የዲኖች፣ ም/ዲኖች፣ የማታ ትም/ስልጠና አስተባባሪ እና ስልጠና ዘርፍ ኃላፊዎች ወርሀዊ ክፍያ ሰዓት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

| ተ.ቁ | በማታ ት/ሥልጠና ተሣታፊ የሚሆን ክፍል/መደብ | የተሣታፊ ሠራተኛ ብዛት | ለወር የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የኮሌጁ ዲን | ዲን | 60 |
| 2 | የትም/ስልጠና ቡድን መሪና ም/ዲን | ም/ዲን | 60 |
| 3 | ኢን/ኤክስቴንሽን ቡድን መሪና ም/ዲን | ም/ዲን | 50 |
| 4 | የማታ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪ | 1 ስልጠና አስተባባሪ | 50 |
| 5 | የማታ ትም/ስልጠና ዘርፍ ኃላፊዎች | 1 ሴክሽን | 10 |
| | | 2 ሴክሽን | 12 |
| | | 3 ሴክሽን | 15 |
| | | 4 ሴክሽን | 18 |
| | | 5 ሴክሽን | 21 |
| | | 6 ሴክሽን | 24 |
| | | 7 ሴክሽንና | 27 |
| | | 7 ሴክሽንና በላይ | በሴክሽን 1 ሰዓት እየጨመረ ይሄዳል |
| 6 | ሾፕ ረዳት | 1 ሴክሽን | 25 |
| | | 2 ሴክሽን | 28 |
| | | 3 ሴክሽን | 32 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 4 ሴክሽን | 35 |
| | | 5 ሴክሽን | 38 |
| | | 6 ሴክሽን | 40 |
| | | 7 ሴክሽን | 42 |
| | | 8 ሴክሽን | 44 |
| | | 9 ሴክሽን | 46 |
| | | 9 ሴክሽንና በላይ | በሴክሽን 1 ሰዓት እየጨመረ ይሄዳል |

11.2 ለድጋፍ ሰጪ የአስተዳደር ሠራተኞች የሚደረግ ክፍያ

- ድጋፍ ሰጪ የአስተዳደር ሠራተኞች በየወሩ ክፍያ ሊፈፀምላቸው የሚችለው ከማታ ትምርትና ስልጠና አጠቃላይ ገቢ ከተሰበሰበው 10 ፐርሰንት ውስጥ ሲሆን ወርሃዊ ክፍያ የሚወሰነው እንደየሥራ ክፍላቸው የሥራ መጠን፣ ክብደትና ስፋት ታይቶ ኮሌጁ በራሱ እንደስራው ሁኔታ በቀጥታ በስራው ላይ መሳተፍ አለባቸው ብሎ ያመነባቸውን የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን ከላይ ከጠቅላላ ገቢው የተጠቀሰውን 10 ፐርሰንት በማኔጅመንቱ አስወስኖ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የቅጣት ድንጋጌዎች

12. ከማሠልጠን ሥራ የሚቀሩ አሠልጣኝ መምህራንን በተመለከተ

12.1 አሠልጣኝ መምህር አሳማኝ ምክንያት ኖሮት በፈቃድ ቢቀርና ያባከነውን ክፍለ ጊዜ ማካካሱ በተጨባጭ ሲረጋገጥ ብቻ ክፍለ ጊዜው ይመዘገብለታል፣

12.2 ያለበቂ ምክንያት እና ያለፈቃድ ከማታ ሥልጠና ላይ የቀረ አሰልጣኝ መምህር የቀረበት ክፍለ ጊዜ ይቆረጥበታል፤ የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያም በጽሑፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፣

12.3 ያለበቂ ምክንያትና ሳያስፈቅድ የቀረ አሰልጣኝ መምህር ያባከነውን ክፍለ ጊዜ የማካካስ ግዴታ ቢኖርበትም ላካካሰው ክፍለ ጊዜ ግን ክፍያ አይኖረውም፤

12.4 በተደጋጋሚ ከማታ የሥልጠና ሥራ ላይ የሚቀር አሠልጣኝ ከስህተቱ የማይታረም ከሆነ ራሱን እዲያሻሽል ለአንድ ዓመት ከሥልጠና ሥራ ላይ ይነሳል /ይታገዳል/፤

12.5 ከአንድ ዓመት እገዳ በኋላ ወደ ማሰልጠኑ ሥራ የተመለሰ መምህር ከነበረው ችግር የማይታረም ከሆነ ከማታው የማሠልጠን ሥራ ላልተወሰነ ጊዜ ይታገዳል፤

12.6 በሥልጠና መጀመሪያ ላይ በሰዓቱ ወደ ማሠልጠኛ ክፍል የማይገባና የማጠናቀቂያ ሰዓት ሳይደርስ ሠልጣኞችን የሚሸኝ/የሚለቅቅ መምህር ያባከናቸው ደቂቃዎችና ሰዓቶች ተደምረው በወሩ መጨረሻ የሚቆረጥ ሆኖ ማስጠንቀቂያም በጽሑፍ ይደርሰዋል፤ ሊታረም ካልቻለ ከማታ ትምህርትና ስልጠና ማስልጠን ሥራ ሊነሣ ይችላል።

13. ሥራቸውን በአግባቡ የማይወጡ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በተመለከተ

13.1 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የዓመት እረፍት ሲወጡ ሥራቸውን ተክቶ የሚሠራ ሰው

በጽሑፍ ለማታ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፤ ክፍያውም ሥራውን ተክቶ ለሠራ ሰው የሚፈፀም ይሆናል፣

13.2 በማታው ተሣታፊ የሆነ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ በተደጋጋሚ ከሥራው የሚቀር

ከሆነና ማስጠንቀቂያ ተሠጥቶትም የማይታረም ከሆነ የማታው ክፍያ አይፈጸምም፤

13.3 ሥራን በተደጋጋሚ በመበደል የታገደ ሠራተኛ የእገዳውን ጊዜ ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ሥራ መመለስ የሚችለው ለተቋሙ ሃላፊ በጽሑፍ ሲያመለክትና ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ይሆናል።

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ደንቦች

- ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም ወጥቶ ለተወሰነ ጊዜ ይሰራበት የነበረው የማታ ትምህርት የተመለከቱ ጉዳዮች ከዚህ በኋላ ከዚህ መመሪያ ውጭ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡
- ይህንን የማታ ትምምህርት መመሪያ የሚቃረኑ አሰራሮች፣ ልማዶች ወይም ውሳኔዎች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 15. መመሪያው የሚፅናበት ጊዜ

ይህ የማታ ትምህርትና ስልጠና መመሪያ በቢሮ ኃላፊ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡